Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

# ፈጣን መመሪያ

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምሕርት ቤቶች (MCPS) የተማሪዎች ሥነ ምግባር ደንብ

**እያንዳንዱ ተማሪ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ደጋፊ፣ እና ምቹ የትምህርት ቤት አውድ ይገባዋል።**

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምሕርት ቤቶች (MCPS) የተማሪዎች ስነምግባር ደንብ ሁላችንም -- እንድንገነዘብ ይረዳናል፦

- ✓ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ባህሪያት
- ✓ የመማር ማስተማር ተግባርን የሚያደናቅፉ ወይም ደህንነትን የሚያውኩ ጣልቃ ገብ ባህሪያት
- ✓ የሚጠበቁ ስነምግባሮች ሳይሟሉ ሲቀሩ ትምህርት ቤቶች እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ
- ✓ ተማሪዎች ከስህተቶቻቸው እንዴት መማር እና ጉዳትን ማረም እንደሚችሉ

የዲሲፕሊን እርምጃ ዓላማው ተማሪዎችን በአዎንታዊ፣ ደህንነቱ በተጠበቀ እና ውጤታማ በሆነ የመማሪያ አካባቢ ስኬታማ እንዲሆኑ ማስተማር፣ ተጠያቂነትን ማስፈን፣ እና መርዳት ነው።

## MCPS ለተማሪዎች የባህሪ ግድፈት እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)፣ የዲሲፕሊን እርምጃ የሚወሰደው ተማሪዎች እንዲማሩ፣ እንዲያድጉ፣ እና የተሻሉ ምርጫዎችን እንዲያደርጉ ለመርዳት ነው። ትምህርት ቤቶች ጉዳትን ለመጠገን፣ ግንኙነቶችን ለማጠናከር፣ እና ተማሪዎችን ተጠያቂ ለማድረግ እንዲሁም ወደፊት እንዲራመዱ እድል በመስጠት የተሓድሶ አቀራረቦችን እና ተራማጅ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ።

ለመጥፎ የባህሪ ድርጊት ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ሰራተኞች ሙሉውን የተፈፀመ ድርጊት ሁናቴ ግምት ውስጥ ያስገባሉ — የተከሰተው ምን እንደሆነ፣ የተማሪው(ዋ)ን ዕድሜ፣ ሌሎች ሁኔታዎችን፣ በሌሎች ላይ የፈጠረውን ተፅእኖ፣ እና ለተማሪው(ዋ) የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ድጋፍ ጭምር በማጤን እርምጃ ይወስዳሉ።

## የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃዎች

| ደረጃ | የእርምጃ አወሳሰድ ምሳሌዎች |
|---|---|
| 1 | ማስጠንቀቂያ፣ የተማሪ ኮንፈረንስ፣ የሚጠበቁ ነገሮችን እንደገና ማስተማር፣ ግብረመልስ፣ የተሐድሶ እርምጃ ውይይት |
| 2 | ከወላጅ ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ እስር፣ ስለ ባህሪ መግለጫ፣ የችግር አፈታት ኮንፈረንስ፣ ወደ ካውንስሊንግ ማስተላለፍ/ሪፈራል |
| 3 | ከት/ቤት አስተዳዳሪ ጋር ኮንፈረንስ ማድረግ፣ ስለ ባህሪ ማሻሻል እቅድ ማዘጋጀት፣ ወደ ተማሪዎች ደህንነት ቡድን ማስተላለፍ/ሪፈራል፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚተገበሩ ጣልቃ ገብነቶች |
| 4 | ለአጭር ጊዜ ከት/ቤት እገዳ ማድረግ፣ የደህንነት እቅድ ማዘጋጀት፣ የወላጅ ኮንፈረንስ፣ እንደገና ወደ ት/ቤት የመመለስ እቅድ መተግበር |
| 5 | ለረጅም ጊዜ ከት/ቤት እገዳ፣ ከት/ቤት ውጭ የሚገኙ አጋሮች እንዲሳተፉ ማድረግ፣ ጠንካራ የባህሪይ ማስተካከያ ጣልቃ ገብነት እቅድ ማዘጋጀት |
| 6 | ለተራዘመ ጊዜ ከት/ቤት ማገድ ወይም ማባረር፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የደህንነት ጥበቃ/የሕግ አስከባሪዎች እንዲሳተፉ ማድረግ፣ ከፍተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ |

## የተለመዱ የተማሪዎች ባህሪያት እና የዲስፕሊን እርምጃ ደረጃዎች

| ባህሪ<br>(የዲስፕሊን መደብ ኮድ) | ምሳሌ | ሊወሰን የሚችል የዲስፕሊን እርምጃ ደረጃ |
|---|---|---|
| ትምሕርት ቤት መከታተል (100) | ከትምህርት ክፍል አቋርጦ መውጣት፣ ማርፈድ፣ ከትምህርት ቤት ያለ ፈቃድ አቋርጦ መውጣት | 1 - 4 |
| አደገኛ እፆች (200) | አደንዛዥ እጾችን፣ አልኮል፣ እና/ወይም በትንፋሽ በመሳብ የሚጨሱ  እጾችን፣ መድኃኒቶችን መያዝ፣ መጠቀም፣ ወይም ማሰራጨት | 2 - 6 |
| የጦር መሳሪያዎች (300) | ተተኳሽ የጦር መሳሪያዎች፣ ቢላዎች፣ BB/pellet ሽጉጦች፣ ከባድ የደህንነት ስጋቶች | 3 - 6 |
| ጥቃት መፈፀም/ማስፈራራት/መደባደብ (400) | ጉልበተኝነት፣ ማስፈራራት፣ የሳይበር ጥቃት፣ ትንኮሳ፣ በቡድን መደባደብ፣ አስፈራርቶ ዝርፊያ መፈፀም ወይም መቀማት | 3 - 6 |
| ቃጠሎ ማድረስ/እሳት መለኮስ/ፈንጂዎችን ማጥመድ/መያዝ (500) | በውሸት አላርም ማስጮኽ፣ የቦምብ ማስፈራሪያ፣ እሳት መለኮስ | 4 - 6 |
| ጾታዊ ጥቃት (600) | ወሲባዊ ጥቃት፣ ያልተገባ ተግባር፣ ትንኮሳ | 3 - 6 |
| አክብሮት መንፈግ/ማዋረድ/ማደናቀፍ (700) | አክብሮት የጎደለው ቋንቋ መጠቀም፣ የክፍል ትምሕርት ማስተጓጎል፣ በትምህርት ላይ ጣልቃ በመግባት ማደናቀፍ፣ ስርአትየለሽ አለባበስ | 1 - 6 |
| ሌላ (800) | ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ የንብረት ውድመት፣ ጥሰት<br>ስልኮችን፣ መገልገያ መሳሪያዎችን፣ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነቶችን ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም<br>የአካዳሚክስ ማታለል ወይም ማጭበርበር | 1 - 6 |